# <u>ትብብርና በጋራ መታገል በዓላማና በግብ፤ኢትዮጵያ፣ኢትዮጵያዊነትና አረንጓዴ-ቢጫ-ቀይ ሰንደቅ ዓላማችን፣በብሔራዊ ሕዝብ አንድነት የታጀበና የታነጸ ሲሆን ብቻ ነው።</u>

ከበላይ መታፈሪያ ዶ/ር

ለአገር ወገን መቆም የሚጠይቅ ትብብር በአሀዳዊት ኢትዮጵያ አንድ፣አገር አንድ ሕዝብ፣ ብሔራዊ ጥቅሞች፣ታሪክ፣ባህልና ማንነትን በተረዱና በአወቁ <u>ኢትዮጵያዊ አጀንዳ</u> ነው።

ትብብርና አብሮ በፀረ-ወያኔ መቆምና ለአገር ነፃነት መታገል ተቀዳሚ ተግባር የሚሆነው ኢትዮጵያዊነትን አውቆ በማንነት ሕልውና ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት።

ከግለሰብ፣ ሲቪክ እስከ ፓለቲካ ድርጅት ወያኔን የመቃወሙ ጥረት የሚናቅ አይደለም።ዳሩ ግን ችግሩ ጥረቶቹ ሁሉ ከኢትዮጵያና ከሕዝብ፣ ከአገር ጥቅም አኳያ የተያያዙ አይደሉም። ባለመሆናቸው የተበታተኑና ውጤት አልባ በመሆን ወያኔን ለ25 ዓመታት አገር ፣ሕዝብና ሃብትን እንዲያሰቃይና እንዲበዘብዝ ጠቅሟል።

ይህን በደንብና በቅጡ መገንዘብ ያስፈልጋል።ስለዚህ በተጨባጭ ሁኔታ ውጤት ለማምጣት ትግሉ በሕዝብ ትርታና በአገር ጥቅሞች በኢትዮጵያዊ አጀንዳ ላይ ተመስርቶ የሕዝብ ብሔራዊ አለኝታን ያቀፈ መሆን አለበት።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚፈልገው መላ አገሩን አሀዳዊ ኢትዮጵያን፣ አንድ ሕዝብነቱን፣አብሮነቱን፣ሰላምና ደህንነቱን፣ ብልጽግናውን ነው።ምኞቱ፣ ተስፋውና ሕልውናው ኢትዮጵያዊነት ነው።የፀረ-ወያኔም ዋናው ትግልና ግቡ ይህ የማይበገር ኢትዮጵያዊ መንፈሱ ነው።ስለዚህ **በፀረ-ወያኔ ቆሜአለሁ የሚል ሁሉ ለኢትዮጵያ፣ ለኢትዮጵያዊነት፣ለሕዝብ አንድነትና ለአንድ ሰንደቅ ዓላማ አረንጓዴ-ቢጫ-ቀይ መቆሙን ማረጋገጥ ይኖርበታል።**ይህ እስካልተረጋገጠ ድረስ የጅምላ ትብብርም ሆነ በፀረ-ወያኔ አብሮ መታገልን ብቻ አይቀበልም። ሕዝብ ማንኛውንም ኃይል አያቅፍም።

በወያኔ ሕገ-መንግሥትና ወያኔ በፈጸማቸው ፀረ-አገር፣ ፀረ-ሕዝብ ጉዳዮች ላይ ግልጽና ጥርት ያለ የተቃውሞ አቋም መውሰድና በይፋ መታወጅ አለበት።ነገር ግን ወያኔን ቀይሮ ሕገ-መንግሥቱን፣ የቋንቋ ክልል ድንበርና አንዳንድ ተግባሮቹን መቀጠል የለውጥ እንቅፋት መሆኑን መረዳትና ቁርጥ አቋም መወሰድ አስፈላጊ ነው።

<u>የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬ የጀመረው ትግል የአገር አድን፣የሕዝብ ነፃነት አንድ አገር አንድ ኢትዮጵያዊ ብሔራዊ ሕዝብ፣ ኢትዮጵያዊነት ነው። ወያኔ ከነ ሕገ-መንግሥቱ ይደምሰስ ነው።</u>

ወያኔን ከኢትዮጵያ ለማስወገድ የሚደረግ የትብብር ትግል እጅግ ብርቱና ውስብስብ ስለሆነ ጥንቃቄንና ጥበብ የተሞላበት አመለካከትንና አካሄድን በሰፊው ይጠይቃል።ዛሬ ያለው ትግል ኢትዮጵያን አድን፣ የሕዝባን ነፃነት ይከብር ነው።ትብብርና ትግሉም የሚጠይቀው ይህን በመሆኑ ትብብሩ የሚደረገው

ኢትዮጵያዊ ማንነትን በፅኑ የሚሻ አቋምን  እንጂ፣ ጊዜው ያለፈበት ያረጀና የከሰረ ፓለቲካን የብሄር-ብሄረሰቦች ከፋፋይ ፀረ-ኅብረተብ አስተሳሰብ የሚያራምዱ ስብስብን፣በጠባብ የጎሳና የቋንቋ ክልል የተመረዙን፣አገር ሲያፈርስ፣ሕዝብ ሲያስጨርስ የቆየውን ባንዳ፣ የግል ጥቅም ቀዛፊና አራማጅ ድርጅቶችና ግለሰቦችን ማሰባሰብና ማጀብ አይደለም።የዚህ ዓይነት ትብብር የሕዝብን ትግል የሚያራክስና የሚያቀዘቅ ከመሆኑም ጋር የሕዝብ ትግሉ እንደተፈለገው እንዳይሄ ቀልባሽ ነው።

ይህ እየታወቀ አቋምን ጥርት ባለ ሁኔታ ሳያረጋግጡና ሳይገልጹ ትብብር በሚል የሚሰባሰብ ኃይል ወያኔ ለመውደቅ በተንገዳገደ ወይም በወደቀ ማግሥት በሽምቅ ተዋጊዎች ከኃላህ ዞረው እንደሚወጉህና የሕዝብ ትግሉንም እንዳታስቀለብስ ከወዲሁ አወቀህ ተረዳ።በሽፍንፍን ማንኛውንም ስብስብ በፀረ-ወያኔ ትብብር ስም መቋቋሙ ሽፍን አጀንዳን ከማራመዱም በላይ ሥልጣንን አስቀድሞ በሞኖፖሊ ለመያዝ ያቀደ አካል ያደርጋል።

ትብብሩ የሚፈጠረው ወያኔን ለመጣል በተንቀሳቀሰና ታግሎም ለማሸነፍ ግብታዊ ሕዝባዊ አካላት ለመፍጠርና የኢትዮጵያን አሀዳዊነት ለማረጋገጥ ነው።የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚፈልገውን ውጤት እንዲያገኝ የትግሉ ተባባሪ አካል መሆን፤ አገሩን፣ነፃነቱን፣መሬቱን፣ሃብቱን፣ዜግነቱንና ማንነቱን ለተነፈገና ላጣ፣ ለአንድነትና ለኢትዮጵያዊነት በቁርጠኝነትና በፅናት የትግሉ አጋዥ ሆኖ በቅንነት፣ በመልካም ምግባርና በመርሆ የታነጸ ለአገር ወገን የሕይወት መስዋዕትነት እስከ መክፈል ዝግጁነትን፣ ከጐኑ መቆምና መታገልን ነው።የኢትዮጵያ ሕዝብ በአገራዊ አንድነት፣ ኢትዮጵያዊነት ከተደራጀና ከተመራ ወያኔን በ24 ስዓት ባይሆን በአምስት ቀን ውስጥ ማስወገድ ይችላል።

ስለሆነም የትግሉ ዓላማና ግብ በቶሎ ውጤታማ እንዲሆን በተመለከተ ብዙ በተለያዩ መስኰች ማቅረብ ይቻላል። ነገር ግን ሁለት ዋና ዓላማዎች አጣዳፊ ሆነው ይታያሉ።

1. ከአገር አቅጣጫ ሕዝብን በአንድነት የሚቀሰቅስ፣ የሚያደራጂና ለትግል የሚያሰማራ አካል ከሕዝብ መሀል ውስጥ መፈጠር አለበት።

2. በውጭ አገር ደግሞ የወያኔንና አጋሮቹን፣ የወያኔ መሰል ድርጅቶችን ሊቋቋም የሚችል አንድ ትልቅ ኃይል ማደራጀትና የመገናኛ መስመር ራዲዮ ጣቢያ በማቋቋም ስርጭቱ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲደርስ ማድረግ እጅግ ተቀዳሚና አስፈላጊ ዋና የትግል መሳሪያ ነው።

ይህ በዚህ እንዳለ፤ በእኔ አመለካከት በፀረ-ወያኔ የትብብር ጥሪ፣ በሰከነ ሁኔታ እንወያይ ብቻ በቂ አይደለም። ጥርት ባለ ሁኔታ አቋምና ዓላማ፣ግብና ማንነትን ማሳየት አስፈላጊ ነው።ከሕዝብ ብሔራዊ ትርታና ከአገር ጥቅም ጋር ከተስተካከለ እሰየሁ ተቀባይነት ሊያገኝ ይችላል።

ከዚህ ውጭ ግን አገርና ሕዝብን ሰንደቅ ዓላማን አንድ አድርጐ ለብሔራዊ ጥቅም የሚያታግልና የሚታገል፣ የትግሉ ውጤት ለኢትዮጵያዊ መንግሥት፣ ለሕዝብና የሕግ የበላይነት ብቁ የሚያደርግ ድርጅት መፈጠር አለበት።

ለዚህ ለአገር ወገን መቆርቆርና ተባባሪ በመሆን፣ ጠላትን ለማስወገድ በአንድ አገራዊ ኢትዮጵያ፣ ኢትዮጵያዊነት መንፈስ አብሮ ተባብሮ በእኩልነት በጠነከረ ትስስር ፣የኢትዮጵያን የነፃነት ኩራት ዓርማ አረንጓዴ-ቢጫ-ቀይ ሰንደቅ ዓላማን ከፍ አድርጐ በማውለብለብ፣ በድፍረትና በጀግንነት በቶሎ ጠንካራና

ብርቱ የማይበገር ድርጅት በመፍጠር እስከ ወዳኛው ድረስ በመታገል ወያኔን አስወግዶ የአገር ትንሳኤን ማረጋገጥ ነው።

## ትብብር አድነትንና ግልጽነትን ይጠይቃል ! !

## ትብብር ኃይል ነው ! !

## ኃይልና ያላሰለሰ ፅኑ ትግል ሁሉን ያሸንፋል ! !

## ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ ! ! !

## ምንጊዜም ኢትዮጵያ፣ ኢትዮጵያዊነት አሸናፊ ነው ! ! !

01/26/2016